# ዶ/ር ድረስ ሳህሉ በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገጠር ክላስተር አስተባባሪና ግብርና ቢሮ ሀላፊ መልዕክት



የተከበራችሁ የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ አመራሮች፣ባለሙያዎችና የስራው ባለቤት ለሆናችሁ መላው የክልላችን አርሶ አደሮች ከሁሉ አስቀድሜ ለግብርናው ዘርፍ ተግባራት መሳካት ስታበረክቱ ለቆያችሁት እና በቀጣይም ዋና ዋና የግብርና ስራዎች እንዲሳኩ ለምታደርጉት አበርክቶ ይህን መልዕክት ሳስተላልፍላችሁ ያለኝ ልባዊ ምስጋና እና ታላቅ አክብሮት በክልሉ መንግስት እና በግብርና ቢሮ ስም ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ፡፡

አማራ ክልል በተፈጥሮ ጸጋ የታደለ፣ ሰፊ የቆዳ ስፋት ያለው፣ ታታሪና ትጉህ ህዝብ ያለበት፣ የከርሰ ምድርና የገፀ ምድር ባለቤት የሆነ እና እስከ 2 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሄ/ር መሬት በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት ያለው፣ ሰፋፊ የሚታረስ መሬት ባለቤት እስከ ከ6 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሄ/ር መሬት ሊታረስ የሚችል እና ከ30 ዓይነት በላይ የተለያዩ ሰብሎችን ማምረት የሚችል ስነ ምህዳር ያለበት፣በእንስሳት ሃብት ልማት ብዙ እምቅ አቅም ያለው በአጠቃላይ ክልሉ ለግብርናው ልማት ዘርፍ በርካታ ያልተነካ እምቅ ጸጋዎች የሚገኙበት ክልል ነው፡፡ ይሁን እንጅ በክልሉ ለበርካታ ዓመታት የዘለቀው የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የሰላም እጦት፣ የአየር ንብረት ለውጥ መዛባት ተከትሎ ድርቅና ጎርፍ ፣ዓለማቀፋዊና ቀጠናዊ ችግሮች የሚፈራረቁበት አካባቢ ከመሆኑ የተነሳ የክልሉ ህዝብ ዛሬም እንደ ወትሮው ለከፋ ችግር ሲጋለጥ ቆይቷል፡፡ ይህን ተከትሎም በአሁኑ ወቅት የምግብ ዋስትናቸውን ያላረጋገጡ የህብረተሰብ ክፍሎች ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡

ስለሆነም የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ በክልሉ በ2022 የተሸጋገረ ግብርና በመፍጠር የምግብ ዋስትናው በቤተሰብ ደረጃ የተረጋገጠለት ህብረተሰብ ተፈጥሮ ማየት የሚል ራዕይ ይዞ የተቀናጀ የተፈጥሮ ሃብትና የመስኖ ልማትን መሠረት በማድረግ ከዝናብ ጥገኝነት የተላቀቀ ገበያ መርና ከስነ-ምዕዳር ጋር የተጣጣመ የኩታገጠም አሠራር የሚተከል፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚደገፍ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠትና የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የክልሉን አርሶ አደር የምግብና ሰርዓተ ምግብ ያካተተ የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ለማረጋገጥ ተልዕኮ በመያዝ ሰፊ ርብርብ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ እያደረገም ይገኛል። ባለፉት ዓመታት የሰብል ልማት ዘርፉን በላቀ ደረጃ እና ተከታታይነት ባለው መልኩ ምርታማነትቱን ለማሳደግ ከፍተኛ ርብርብ በመደረጉ ተከታታይነት ያለው የምርት ዕድገት ተመዝግቧል፡፡ ምርታማነት ወደ 32 ኩንታል ማድረስ ተችሏል። ይህ የምርት እድገት የመጣው ሁሉም ባለድርሻ

አካላት በየደረጃው ሁለንተናዊ ድጋፍ ማድረግ በመቻሉ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ባለፉት ተከታታይ ዓመታት የክልሉ የምርት እድገት የሚያበረታታ ቢሆንም ክልሉ ካለው እምቅ ፀጋ፣ የማምረት አቅምና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና አሠራሮችን በተሟላ ሁኔታ በመፈፀም በኩል ተወስዶ ሲታይ አሁንም ገና ሰፊ ስራ መሰራት ይጠበቅብናል፡፡ ስለዚህ የግብርናውን የምርት ዕድገት በዘላቂነት በማስቀጠል የህዝባችንን ፍላጎት በተሟላ ሁኔታ ማርካት ቁልፍ ተግባር ተደርጎ ይሰራል፡፡

ለምርትና ምርታማነት ዕድገት ማነቆ ከሆኑ ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን በወቅቱ፣በመጠን፣በጥራትና በአይነት ለአርሶ አደሩ ማቅረብ ላይ ክፍተቶች ይስተዋላሉ እንዲሁም አዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በተሟላ ሁኔታ በመፈጸም በኩል ውስንነት መኖሩና አርሶ አደሩ አሁን የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ በሚመጥን መልኩ በእውቀት ላይ ተመስርቶና የመፈፀም አቅምን የሚገነባ የክህሎት ድጋፍ በማድረግ በኩል ጉድለት ከመኖሩ ባሻገር የግብርናው ዘርፍ የሁሉም ችግር መውጫ መንገድ መሆኑን በእምነት አለመያዝና ሌሎችም ችግሮች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ስለሆነም ይህን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን በወቅቱ ማቅረብ፣ግብርናን ከኋላቀር አሠራር ሊያላቅቁ የሚችሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች ስራ ላይ እንዲውሉ ጠንክሮ መስራት፣የግብርና ምርቶች የተሻለ ገበያ እንዲኖራቸው የገበያ ትስስር መፍጠር፣ የክላስተር አሠራርን አጠናክሮ ማስቀጠል፣ከዝናብ ጥገኝነት በመላቀቅ በዓመት ከሁለት እስከ ሶስት ጊዜ ለማምረት የመስኖ ልማት በተለይ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት አጠናክሮ ማስቀጠል አማራጭ የሌለው የህልውና ጉዳይ ተደርጎ መስራት አለበት፡፡ በተጨማሪም የግል ባለሃብቶችን ተሳትፎ በላቀ ደረጃ ማሳደግ፣ ተቋማዊ የመስራት ብቃትን ማረጋገጥ፣ ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ስርዓትን መዘርጋት እንዲሁም ከባለድርሻና አጋር አካላት ጋር ያለውን ትስስር ይበልጥ ማጠናከር ላይ ትኩረት ተሰጥተው የሚሰሩ ተግባራት ይሆናሉ፡፡

በክልላችን በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የተገኘው ውጤት አበረታች በመሆኑ ለዘርፉ መነቃቃት አበርክቶው የጎላ ነው፡፡ ባለፉት ዓመታት በተሠራው የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት ስራ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ያደረጉ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ሌላኛው ትልቅ አቅም እና ጸጋ የእንስሳት ሃብታችን ነው፡፡ ዘርፉን የበለጠ ለማነቃቃትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እንደ ሃገር የተነደፈው የሌማት ትሩፋት ተግባር በክልላችንም እየተተገበረ ይገኛል፡፡ ይህን ተከትሎም በከተሞችና በገጠር አካባቢዎች በእንቁላል፣በስጋ፣በወተት፣በማርና በዓሳ ምርት አበረታች ለውጦች ታይተዋል፡፡ የጀመርነውን የሌማት ትሩፋት ተግባር የላቀ ውጤታማ ለማድረግ የሚረዳ የእንስሳት ጤና፣ዝርያ መሻሻልና መኖ ዝግጅት ተግባራትም በትኩረት ተይዘው እየተሰሩ ይገኛል፡፡

የተከበራችሁ መላው የግብርና ባለሙያዎች፣ አመራሮችና ውድ አርሶ አደሮች ባለፉት ጊዜያት ያከናወናቸው ተግባራት የበለጠ ዘላቂ ለማድረግና ውጤታማነት ለማረጋገጥም በቀጣይ ጊዜያትም የላቀ ትኩረት ሰጥተን ልንረባረብ ይገባል፡፡ በተለይም በአማራ ክልል አሻጋሪ እና ዘላቂ ልማትን የሚያመጣ የ25 ዓመት ዕቅድ ታቅዷል። ዕቅዱ በክልሉ ያለውን ፀጋ በመጠቀም የህዝቡን የልማት ተጠቃሚነትና የክልሉን እድገት በዘላቂነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው። ከ25 ዓመት ዕቅዱ መካከል ደግሞ የግብርና ልማት ዕቅድ አንደኛው ነው፡፡ ይህ እቅድ የግብርና ዘርፉን አሁን ካለበት ደረጃ ወደ ላቀ ከፍታ ሊያሻግር የሚያስችል ሆኖ የታቀደ ነው። ዘርፉን በሁለንተናዊ መንገድ ለማዘመን ይቻል ዘንድ መሰረታዊ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል። ከ25 ዓመቱ አሻጋሪ እቅድ የተቀዳ የአምስት ዓመት እስትራቴጂክ እቅድና የአንድ ዓመት እቅድ አቅደናል። ማስፈፀሚያ ስልቶችንም አስቀምጠናል። ከእኛ የሚጠበቀው ወገብን የሚያጎብጥ ስራ ሰርተን አንገታችንን ቀና የሚያደርግ ውጤት ማስመዝገብ ነው። በያዝነው በጀት ዓመት ከተረጅነት ወደ ምርታማነት ለመሻገር ትልቅ ግብ አስቀምጠናል።ግቦቻችን ለማሳካት ከምንም በላይ በየደረጃው ያለው የግብርና ባለሙያና አመራር መላ አርሶ አደሩን በማግኘት ተገቢውን ሙያዊ ድጋፍ መስጠት ይጠበቅብናል፡፡ ይህን ተከትሎም በቀጣይ የጀመርነው የሰብል፣ የመስኖ እና የእንስሳት ሃብት ልማት እንዲሁም የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት ስራዎቻችን ቁልፍ የትኩረት ማዕከል አድርገን በመያዝ በላቀ ውጤት ለመፈፀም ብርቱ ጥረት ማድረግ ከሁሉም ይጠበቃል፡፡ በመጨረሻም ሁሉም የግብርና ቤተሰብ የግብርና ስራችን ፋታ የማይሰጥ መሆኑን በመረዳት የሚያጋጥመንን ጊዜያዊ ፈተናዎችን ሁሉ በመቋቋም እያንዳንዱን ተግባር በጥብቅ ዲሲፕሊን፣ በታላቅ ሀላፊነትና በላቀ ትጋት በመፈፀም የጀመርነውን የብልፅግና ጉዞ ለማሳካት የተቀናጀ እርብርብ እንድናደርግ አክብሮታዊ ጥሪ ላቀርብላችሁ እወዳለሁ፡፡

## ደረጀ ማንደፍሮ
## የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ቢሮ ሀላፊና የተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ አስተባባሪ መልዕክት



ተፈጥሮን መጠበቅና መንከባከብ ለሰው ልጅ የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን አማራጭ የሌለው የህልውና ጉዳይ ነው። ምክንያቱም የሰው ልጅ ተፈጥሮን በጠበቀና በተንከባከበበት ልክ፣ ተፈጥሮም ለሰው ልጅ የሚሰጠው ፀጋ እጅጉን ከፍ ያለ ነው። ካልሆነም ውጤቱ በተቃራኒው የሚገለጽ ነው። ለዚህ ዋናው ማሳያው ደግሞ ዛሬ ላይ ዓለምን በእጅጉ አስጨንቆ የያዛት የአየር ንብረት ጉዳይ ነው። ይህ የሰው ልጅ ሰው ሰራሽ ችግር ታዲያ መልሶ የሰው ልጅን አንዴ በድርቅ፣ሌላ ጊዜ በጎርፍ፣ ሲሻውም በወጀብ እያንሳቀለው ይገኛል። አማራ ክልል የበርካታ አየር ንብረትና የአየር ንብረት ቀጠና ፣ የማራኪ መልክዓ ምድር፣ የከርሰ ምድርና የገፀ ምድር ውሃ ባለቤት፣ ለእርሻ ምቹና ተስማሚ ስነ ምህዳር ያለው ክልል ነው። የክልሉ እርሻ መሬት ለብዙ ሽህ ዓመታት ሲታረስ የቆየ በመሆኑ በሂደት የአፈር መሸርሸርና ለምነት መቀነስ፣ የደኖች መመናመን፣ መጠኑና ስርጭቱ ያልተስተካከለ የዝናብ ስርጭት፣ የህዝብ ቁጥር እድገት ተጨምሮበት የአካባቢ መራቆት ሲያስከትል ቆይቷል። ተፈጥሮን መጠበቅና መንከባከብ ባለመቻላችን በግብርና ዘርፉ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳረፉ አልቀረም። የአየር ንብርት ለውጥ በተከሰተ ቁጥር ክልሉ ለጎርፍ እና ለድርቅ ተጋላጭ ሲሆን ቆይቷል። የአካባቢ መራቆትና መመናመን በሂደት በግብርና ምርትና ምርታማነት ላይ በግልፅ የሚታይ አሉታዊ ተፅእኖ አሳርፏል።

ይህን ነባራዊ ሀቅ በመገንዘብና እንዲሁም የሀገሪቱን የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን መሰረት በማድረግ የክልሉ ግብርና ቢሮ የተፈጥሮ ሀብትን በማልማትና በመጠበቅ ወደ ነበረበት ለመመለስ የሚያስችል ስልቶችና አቅጣጫዎችን በመንደፍ መላ ህዝቡን በተለይም አርሶ አደሩን በማሳተፍ ሲሰራ ቆይቷል። የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ስራ በክልሉ መንግስት እና ህዝብ የህልውና ጉዳይ ነው የሚል አቋም በመወሰዱ መላ ህዝቡ በፍላጐት ያለምንም ክፍያ በየዓመቱ እየተመመ ሲሰራ ቆይቷል፣ እየሰራም ይገኛል።

የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም መዳረሻ ግቡ ተፈጥሮ ሀብትን አልምቶ የሚቆም ሳይሆን ለግብርና ልማት መሰረት መጣል ነው። የሰብል፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የእንስሳት ሀብት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የህብረተሰቡን የልማት አማራጮች በማስፋትና በማሳደግ ኑሮውን ማሻሻል ነው

በክልሉ የተፋሰስ ልማት ዘላቂነትን ለማረጋገጥ ከተፋሰስ ተጠቃሚ ማህበረሰብ ጋር በመመካከር በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። የተፋሰስ ተቋም ግንባታ ተጠቃሽ ተግባር ነው። የክልሉ አብዛኛው ተፋሰሶች የራሳቸው ጽ/ቤተ ያላቸው ሲሆን በክልሉ ምክር ቤት ፀድቆ ስራ ላይ የዋለው የተፋሰስ ደንብ ለተፋሰስ

ተጠቃሚነትና ዘላቂነት ትልቅ አስተዋጽኦ ተወጥቷል። ማህበረሰቡን በባለቤትነት ባሳተፈ መልኩ በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች ተግባራዊ የተደረገው የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ አበረታች ውጤት ማየት ተችሏል። ይህ የተፋሰስ ልማት ስራው ውጤታማ እንዲሆን ህብረተሰቡን በተለይ አርሶ አደሩን የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራዎችን ጥቅም እንዲረዳ በማድረግ ልማቱን በባለቤትነት እንዲያከናውን ማድረግ ተችሏል። የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት ስራዎች በመሰራታቸው፣ የተራቆቱና የተጎሩረዱ የወል መሬቶች ከመጠገናቸውም ባሻገር የአፈር ክለት ቀንሷል፣ ከዓመት ዓመት የሰብል ምርትና ምርታማነት ጭማሪ አሳይቷል፣ ምንጮች እንዲጎለብቱ በመደረጉ እና ለመስኖ ልማትም ምቹ ሁኔታ በመፈጠሩ የክልሉ አርሶ አደሮች በዓመት እስከ ሶስት ጊዜ ማምረት ጀምረዋል። ከዚህ ቀደም መስኖ ተጠቃሚ ያልነበሩ አርሶ አደሮች አሁን ላይ የልማቱ ተጠቃሚ መሆን ጀምረዋል። ባለፉት ዓመታት በክልሉ የተከናወነው የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ ግድቦች በደለል እንዳይሞሉ አድርጓል። በተለይም የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ከተጀመረ ወዲህ ለተፋሰስ ልማት ስራዎች በተሰጠው ትኩረት ግድቡ በደለል እንዳይሞላ የአባይ እና የተከዜ ተፋሰሶች በሚገኙባቸው የክልሉ አካባቢዎች ላይ በልዩ ትኩረት የማልማት ስራ በመሰራቱ ግድቡን ከደለል መታደግ ተችሏል።

ሌላኛው ቁልፍ ተግባር ደግሞ የአረንጓዴ አሻራ ስራችን ነው። መርሃ ግብሩ እውን ከሆነበት ከ2011 ዓ/ም ጀምሮ በተተከሉት ችግኞች እንደ ክልል ዘርፈ ብዙ ትሩፋቶች ተገኝተዋል። የክልሉን የደን ሽፋን 16 ነጥብ 3 በመቶ ከመድረሱም ባሻገር የአየር ንብረቱ የተረጋጋና ለግብርና ስራም አመቺ ሁኗል። እንደሚታወቀው አረንጓዴ አሻራ ኢኮኖሚ ነው። የተለያዩ ምርቶችን ምርታማነት በመጨመር በምግብ ራስን ከመቻል ባሻገር የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ የግብርና ምርቶች ምርታማነት ጨምሯል። እየተካሄደ ያለው የችግኝ ተከላ መርሃግብር ክልሉን በአረንጓዴ ከማልበስ ባሻገር የችግኝ ተከላን ከግብርና ጋር በማቀናጀት ማካሄድና አቮካዶን እንዲሁም ማንጎና ፓፓያ የመሳሰሉ ፍራፍሬዎችን ጨምሮ የተለያዩ ችግኞች እንዲተከሉ ያስቻለና በጥቂት ዓመታት ውስጥ ለምግብነት የሚውሉ ናቸው። ይህም በምግብ ራስን እንድንችልና ከተረጅነት እንድንላቀቅ በማድረግ ረገድ ፋይዳው የጎላ ነው።

ከአረንጓዴ ትሩፋቶች መካከል አንዱ ለዘመናት እየታጠበ ወደ ጎረቤት ሀገራት የሚሄደውን አፈር መቀነስ መቻሉ ነው። መረጃዎች እንደሚያሳዩት የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር እንደ ሀገር መተግበር ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በዓባይ ተፋሰስ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ችግኞች እየተተከሉ በመሆኑ ለዘመናት ለጎረቤት ሀገራት ሲሳይ ሲሆን የኖረውን የአፈር ሀብታችንን ለመጠበቅ አስችሎናል። እነዚህ ሁሉ የአረንጓዴ አሻራ ትሩፋቶች ሲደማመሩ ኢትዮጵያ እንድታንሰራራ የሚያደርጉና የብልፅግና መሰረቷን የሚተክሉ ናቸው። ለመጭው ትውልድም የተሻለች ሀገር ለማውረስ የሚያስችል ነው።

# ቃልኪዳን ሽፈራው
# የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ቢሮ ሀላፊና
# የእርሻና ሆርቲካልቸር ዘርፍ አስተባባሪ መልዕክት




አማራ ክልል ታታሪ አርሶ አደሮች፣ ሰፊ የሚታረስና ለም መሬት፣ እምቅ የውሃ አቅም፣ ለግብርና ስራ ተስማሚ ስነ ምህዳር ያለው ነው።የግብርና ዘርፉ ለክልሉ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እድገት 54 በመቶ ድርሻ ያለው ነው። ትልቅ ድርሻ ያለውን የክልሉን ግብርና ማዘመን፣ ማሸጋገር ደግሞ ምን ያህል ለክልሉ ኢኮኖሚያዊ እድገት አስተዋፅኦ እንዳለው መገንዘብ አያዳግትም። በተለይ ሰብል ልማት የአማራ ክልልን ሁለንተናዊ እድገት የሚወስን በመሆኑ የአካባቢን ስነ-ምህዳር መሰረት ያደረገ፣ ተስማሚ የሰብል ልማትና ጥበቃ ቴክኖሎጂዎችን አሟልቶ መጠቀም ያስፈልጋል። ዋና ዋና የምግብ፣ የኢንዱስትሪና የኤክስፖርት ሰብሎችን በስፋትና በጥራት በማምረት የክልሉን ኢኮኖሚ የማሳደግና የአርሶ አደሩን ህይወት የመቀየር ሀላፊነት አለብን። ስለሆነም የክልላችን የኢኮኖሚ እድገትና የህበረተሰቡ ተጠቃሚነት በዋናነት የሚወሰነው በሰብል ልማት ስራችን በመሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት መጠቀም፣ አሰራሮችን ማዘመን፣ የግብዓትና የሜካናይዜሽን አጠቃቀም ማሳደግ በአጠቃላይ የሙሉ ፓኬጅ ትግበራ ለምርት ጭማሪ ወሳኝ ሚና ያለውን መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

የክልሉ ግብርና ቢሮ ለግብርናው ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በአንድ በኩል የምግብ ዋስትናችንን አረጋግጠን ከተረጅነት ለመላቀቅ በሌላ በኩል ለአግሮ ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃ በስፋት ለማቅረብ እንዲሁም የኤክስፖርት ሰብሎችን በማምረት ለውጭ ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከድህነትና ከተረጅነት የመውጣት አቅጣጫን ይዞ እየሰራ ይገኛል። በዚህ ረገድ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል። የኩታገጠም እርሻ ማስፋፋት፣ ምርጥ ዘርና የአፈር ማዳበሪያ፣ በመስመር መዝራት፣ ፀረ አረምና ፀረ ተባይ መድሀኒቶችን መጠቀም ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ የግብርና ፓኬጆች ምርታማነት እንዲያድግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ለመስኖ ልማትም ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው። ከግብርና ዘርፉ መሠረታዊ አቅጣጫዎች መካከል አንዱ የመስኖ አቅምን በማጎልበት የግብርና ዘርፉን ከዝናብ ጥገኝነት ማላቀቅ ሲሆን በክልሉ በመስኖ ልማት ከፍተኛ ለውጥ ለማምጣትም በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል። በመስኖ ልማት እምርታዊ ለውጥ ለማምጣት ሁሉም የክልሉ አርሶ አደሮች ቢያንስ አንድ የመስኖ ውሃ አማራጭ እንዲኖራቸው ለማድረግ ከፍተኛ እርብርብ ማድረግ አለብን እያልኩ መልዕክቴን አስተላልፋለሁ።

## አጀበ ስንሻው

## የምክትል ቢሮ ሀላፊና የግብርና  ግብዓትና የገጠር ፋይናንስ አቅርቦት ዘርፍ አስተባባሪ መልዕክት



የሀገራችን ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆነውን የግብርና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ፤ የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ዘርፉን የማዘመንና በቴክኖሎጂ የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ይገኛል። ግብርናው ከኋላቀር አሠራር ወጥቶ በቴክኖሎጂ የሚደገፍ አድርጎ የሀገርን ኢኮኖሚ እንዲገነባ የአፈር ማዳበሪያ፣ የምርጥ ዘር፣ የኮምባይነር፤ የትራክተርና መሰል ግብዓቶችን የማቅረብ ሥራ እየተሠራ ነው። የአፈር ማዳበሪያ ለታለመለት ዓላማ በማዋል ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ነው። የግብርናውን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እየተሠሩ ካሉ ሥራዎች መካከል አንዱ የአፈር ማዳበሪያን ለአርሶ አደሩ በበቂ ሁኔታ ተደራሽ የማድረግ ሥራ ነው። የአማራ ክልልን የግብርና ምርታማነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ  የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ የማድረግ ሥራ ተሰርቷል። አርሶ አደሩ የአፈር ማዳበሪያን የመጠቀም ባህሉ ከዓመት ወደ ዓመት እየያደገ በመምጣቱ ይህንኑ ፍላጎት ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። እየተደረገም ይገኛል። በግብር ዘርፉ ላይ እየተሠራ ያለው የማዘመን፤ በቴክኖሎጂ የማስደገፍ ሥራ እንዲሁም የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ስርጭት ፍትሀዊ ለማድረግ እና ህገ ወጥነትን ለመከላከል የህግ ማዕቀፎች ተዘጋጅተው ስራ ላይ ውለዋል። ባለፉት ዓመታት በግብርና ግብዓቶች አቅርቦት፤ ስርጭትና አጠቃቀም የነበሩ መሠረታዊ ችግሮችን  በመፍታት ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ ተሰርቷል።

አብዛኛው አርሶአደር የሚከተለውን ኋላቀር የግብርና አመራረትና አሰራር ስር ነቀል በሆነ መልኩ ለመለወጥና የተያዘውን የልማት ግብ ማሳካት ይቻል ዘንድ በክልሉ ግብርና ቢሮ በኩል የተጀመረው ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል። በተለይም በምግብ ሰብል ራስን ለመቻል የሚደረገው ጥረት እውን መሆን የሚችለው በመካናይዜሽን የተመራ ግብርና ማስፋፋት ሲቻል እንደሆነ ለሁላችንም ግልፅ ነው። አብዛኞቹ በምጣኔ ሀብታቸው ያደጉ ሀገራት ግብርናቸውን በሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ እንዲመራ በማድረጋቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ምርታማነታቸውን ከፍ ያደርገዋል። ከራሳቸው አልፈው ሌሎችን መመገብ ችለዋል። በአንፃሩ ደግሞ በሀገራችን ሆነ በክልላችን ምንም እንኳ ሰፊና ለእርሻ የሚሆን መሬትና ተስማሚ የአየር ንብረት ቢኖርም የምትከተለው ኋላቀር፣ በሰው ጉልበት ላይ የተመሰረተ ግብርና በመሆኑ ምርትና ምርታማነት የሚፈለገውን ያህል ደረጃ ገና አልደረሰም። በዚህ ምክንያት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ አልተቻለም። ችግሩን ለመፍታት ከባለድር አካላት ጋር ተቀናጅተን እየሰራን ነው። በተለይም ከእርሻ ሜካናይዜሽን አቅርቦት አኳያ ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በጋራ እየሰራን ሲሆን

አርሶ አደሩ ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎች ተጠቅሞ የማረሱ ልምምድ በጥሩ ጅማሬ ላይ ይገኛል። ለዚህ ደግሞ በክልሉ እየተገበረ ያለው የክላስተር እርሻ አሰራር ዘዴ አርሶአደሩ ተደራጅቶ በዘመናዊ መንገድ እንዲያመርት የሚያደርገው በመሆኑ አጠናክረን እናስቀጥለዋለን።

የግል ባለሀብቱ ለግብርና ዘርፉ እድገት የማይተካ ሚና አለው። እነዚህ ቁልፍ የግብርና ባለድርሻ አካላት ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን ከማልማት ባሻገር የአርሶ አደሩ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር አቅም ሆነው እንዲያገለግሉ የክልሉ ግብርና ቢሮ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ እየገለፅኩ የግል ባለሀብቶችም ለሀገርና ለህዝብ ተጠቃሚነት ሲባል መከፈል ያለበትን ዋጋ ከፍላችሁ ከድህነት ለመውጣት በታላቅ ሀላፊነት እንድትሰሩ ጥሪየን አስተላልፋለሁ።

## ስለሽ ሙሉነህ

## የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ጽ/ቤት ሀላፊና የአስተዳደር ዘርፍ አስተባባሪ መልዕክት



የአማራ ክልል ግብርና ቢሮን ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ ግብ እና ዓላማ ለማሳካት የቢሮው የአስተዳደር ሰራተኞች ትልቅ ሚና አላቸው። ለዓላማ ፈፃሚ ባለሙያዎች ምቹ የስራ ሁኔታ በመፍጠር ረገድ በአስተዳደር ስራተኞች በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል። የአገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የተገልጋይ ደንበኞችን እርካታ ለማረጋገጥ የሪፎርም ስራዎች በስፋት ተተግብረዋል። መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። አሰራሮችን ለማዘመን ዲጅታላዜሽን ተግባራዊ እየተደረገ ነው። በሰው ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬትና በንብረት ክፍል የተጀመረው የዲጅታላይዜሽን አሰራር ከፍተኛ ለውጥ አምጥቷል። በሌሎች የአገልግሎት ዘርፎችም ተጠናክሮ ይቀጥላል።

በአስተዳደር ዘርፍ ያሉ ዳይሬክቶሬቶች ማለትም የሰው ሀብት ልማት፣ የእቅድ በጀት ዝግጅት ክትትልና ግምገማ፣ የግዥ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር፣ የለውጥ ስራዎች ክትትልና ድጋፍ፣ የውስጥ ኦዲት፣ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጅ እና የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት የተለያየ ተግባርና ሀላፊነት ቢኖራቸውም መዳረሻ ግባቸው ግን የግብርና ቢሮን ራዕይና ተልዕኮ ማሳካት በመሆኑ ከመቼውም ጊዜ በላይ ለጋራ ውጤት በጋራ ተቀናጅቶ መረባረብ ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ የአስተዳደር ዘርፉ ከተሰጠው ተልዕኮ አኳያ ትልልቅ ስራዎችን መስራት ይጠበቅብናል። ስለሆነም ከፍተኛ እርብርብ የሚጠይቁ ተግባራትን ለይተን፣ ቅንጅታዊ አሰራርን በማስፈን እንድንሰራ እንዲሁም የአስተዳደር ሰራተኞች ለተቋሙ ግብ ስኬት የጎላ አበርክቶ እንዳላችሁ በመገንዘብ የበኩላችሁን ድርሻ እንድትወጡ ከታላቅ አደራ ጋር መልዕክቴን አስተላልፋለሁ።